PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር
Ref.No [illegible]/5/2008
ቀን
Date 2/5/2008

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 41/2007 በሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው ሆኖ መደበኛውን (አውቶማቲክ) አውቶሞቢል የማሽከርከር ብቃት ያላቸው አካል ጉዳተኞች ዋጋው ከፍተኛ የሆነውን ልዩ ተሽከርካሪ እንዲያስገቡ ማስገደድ ተገቢ ባለመሆኑ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ የመመሪያውን ማሻሻያ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አብዱልአዚዝ መሐመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ
ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

ስልክ
Tel 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ.
P.O.Box 1905,1037
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24 55 14 98
251-11-155 11 48

እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

# አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ <u>ቁጥር 41/2007 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ</u>

አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 41/2007 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

2. <u>ማሻሻያ</u>

   አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

   የመመሪያው አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል።

   (1) የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት ሆኖ ለማሽከርከር አካላዊ ችሎታ እና የማሽከርከር ብቃት ያለው አካል ጉዳተኛ ከሆነ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ አንድ ባለሁለት እግር ወንበር ወይም ባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ልዩ አውቶሞቢል ወይም መደበኛ አውቶሞቢል፣ ወይም

3. <u>ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን</u>

   ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

*አዲስ አበባ ጥር 2 ቀን 2008 ዓ.ም*

*አብዱልአዚዝ መሐመድ*
*የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር*

Amend.Dire.W/GT